የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የውጪ የምርጫ ታዛቢዎች ፍቃድ አሰጣጥ፣ የአሠራር ሥርዓት እና የሥነ ምግባር መመሪያ

# ቁጥር 11/2013

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 116 ንኡስ አንቀፅ (2)፣ አንቀፅ 117 እና አንቀፅ 163 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል::

### አንቀጽ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የውጪ የምርጫ ታዛቢዎች መመሪያ ቁጥር -----/2013"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፦

1) **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።።
2) **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3) **"የውጪ ምርጫ ታዛቢ ቡድን"** ማለት (ከዚህ በኋላ **"የታዛቢ ቡድን"** እየተባለ የሚጠራው) አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት በመንግስት ምርጫን እንዲታዘቡ የሚጋበዙ መንግስታት ወይም አለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ ተቋማት

እንዲሁም በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡

4) **"የመታወቂያ ካርድ"** ማለት አንድ ምርጫን ለመታዘብ የተፈቀደለት የውጪ የምርጫ ታዛቢ ወይም የቡድን አባል የምርጫ ሂደትን ለመታዘብ የሚያስችለው በቦርዱ የሚሰጥ የፈቃድ ካርድ ነው፡፡
5) **"ተጠሪ"** ማለት ለቦርዱ የፈቃድ ማመልከቻ ያቀረበ አንድ የውጪ ምርጫ ታዛቢ ማንኛውንም ሰነድ ወይም መልዕክት ከቦርዱ እንዲቀበል፣ መልዕክት እንዲልክ ወይም በሰነድ ላይ እንዲፈርም አግባብ ባለው የመንግስት አካል በተረጋገጠ ሰነድ የሚወክለው ሰው ነው፡፡
6) **"ታዛቢ"** ማለት የውጪ ታዛቢ ድርጅትን ወይም ተቋምን በመወከል ምርጫን እንዲታዘብ በቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡
7) **"የውጪ ታዛቢ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ"** ማለት የውጪ ታዛቢውን ተቋም ስራ ለማገዝ በታዛቢው የሚቀጠር አሽከርካሪ፣ የትርጉም ሰራተኛ፣ የጽህፈት ስራ የሚሰራ ጸሃፊ እና ሌላ ከመታዘብ ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስራ የሚያከናውን ሰው ሲሆን በማንኛውም መልኩ በመታዘብ ሰራ ላይ ተሳትፎ ሊያደርግ አይችልም፡፡
8) **"የምርጫ ሂደት"** ማለት የመራጭ ምዝገባ፣ የእጩ ምዝገባ፣ የምርጫ ቅስቀሳ፣ የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነት፣ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ፣ ጊዜያዊ ውጤት አደማመር፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት እና የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ማሳወቅን የሚያካትት ነው።
9) የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በአዋጁ ላይ የተሰጠ የቃላት ትርጉም ለዚህ መመሪያ ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት በኢትዮጵያ መንግስት ግብዣ መሠረት በቦርዱ የውጪ ታዛቢነት ፈቃድ አግኝተው ምርጫን በሚታዘቡ መንግስታት፣ ተቋማት ወይም ድርጅቶችና ወኪሎቻቸው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀፅ 5. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 6. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የምርጫ ሂደት ተአማኒነት ለማረጋገጥና የውጪ ታዛቢዎችን ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና ሥነ ምግባርን መወሰን ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>የጥያቄ አቀራረብ እና ፍቃድ አሰጣጥ ሥርዓት</u>

**አንቀጽ 7. የውጪ የምርጫ ታዛቢዎችን ስለ መጋበዝ**

1. መንግስት በአዋጁ አንቀፅ 114 ንኡስ አንቀፅ (2) መሠረት በውጪ ጉዳይ ሚንስቴር በኩል ታዛቢዎችን በመጋበዝ ምርጫን እንዲታዘቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ባደረገው ጥሪ መሠረት ለመታዘብ የተመዘገቡ ታዛቢዎችን ዝርዝር መረጃ ቦርዱ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ ሞልቶ ለቦርዱ ያስተላልፋል።
3. ቦርዱ ፈቃድ የሚሰጠው በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋባዥነት ማመልከቻ ላቀረቡ እና ከውጭ ጉዳይ የመጀመሪያ ፈቃድ አግኝተው ወደ ምርጫ ቦርድ የተላለፉ ታዛቢዎች ብቻ ነው፡፡
4. በግለሰብ ደረጃ የሚሰጥ የታዛቢነት ፈቃድ አይኖርም፡፡ ሆኖም አንድ ፈቃድ የተሰጠው ታዛቢ ተቋም ወይም ቡድን ስር ተመዝግቦ ቡድኑን ወክሎ እንዲታዘብ የታዛቢነት መታወቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 8. የውጪ ታዛቢ ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ**

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተጋበዙ የውጪ ታዛቢዎች በቦርዱ የተዘጋጀውን የፍቃድ ወረቀት ለማግኘት የሚያስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎችን የያዘ ቅጽ በመሙላት ለምርጫ ቦርድ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ተጋባዥ ታዛቢዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት የሞሉትን ቅፅና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተዘረዘሩትን ሰነዶች ለቦርዱ እንደደረሰው በደብዳቤ ይገልጽላቸዋል፡፡

3. አንድ ታዛቢ ተቋም ወይም ቡድን ለራሱ ከሚያቀርበው የፍቃድ ማመልከቻ በተጨማሪ ለሚያሰማራው ታዛቢ የታዛቢነት መታወቂያ እንዲሰጥ ለቦርዱ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ቦርዱ አስፈላጊ ነው የሚለውን ተጨማሪ መረጃ ወይም ማስረጃ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
5. ቦርዱ ውሣኔውን ለምርጫ ታዛቢ ተቋም ወይም ቡድን በአካል፣ በኢሜይል፣ በፋክስ ወይም በአደራ ደብዳቤ ያሳውቃል፡፡
6. ታዛቢዎች ቅፆች በትክክል መሞላታቸውን፣ አግባብ ያላቸው አባሪ ሰነዶች መያያዛቸውን እንዲሁም እነዚህ ሰነዶች በትክክለኛ አድራሻ መላካቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
7. አንድ ታዛቢ አዋጁንና ይህንን መመሪያ፣ በቦርዱ የተዘጋጀ የሥነ ምግባር ደንብ ለማክበር መስማማቱን ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ በመፈረም ካረጋገጠ በኋላ ቦርዱ ታዛቢውን በመመዝገብ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

## አንቀጽ 9. ታዛቢ መሆን ስለሚችል ሰው

የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን በታዛቢነት የሚያሰማራው ሰው፡-

1. ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነ፣
2. የታወቀ የሥነ ምግባር ብልሹነት የሌለው ወይም በከባድ ወንጀል ተጠርጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የማይፈለግ ወይም ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያልተደረገ፣
3. ከማንኛውም በምርጫው የሚወዳደር የፖለቲካ ፓርቲወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ጋር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ወይም ሌላ ማንኛውም የጥቅም ግንኙነት ወይም ግጭት የሌለው፣
4. በሀገር ውስጥ ባለ የፖለቲካ ጉዳይ፣ አንድን የፖለቲካ ፓርቲ አቋምን፣ ቡድንን ወይም የፖለቲካ ፓርቲን በተመለከተ ወገንተኝነት የማያንፀባርቅ፡፡
5. የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር መመሪያ የፈረመ መሆኑን ከሚያስገባው ማመልከቻ ጋር በፅሁፍ በማስፈር ማረጋገጫ የሰጠ መሆን አለበት፡፡

### አንቀጽ 10. የውጪ ታዛቢ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ፈቃድ

1. አንድ የውጪ ታዛቢ ቡድን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ለመቅጠር ሲፈልግ ቦርዱ ፈቃድ እንዲሰጠው በጽሁፍ ማመልከት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ያመለከተ ታዛቢ የሚቀጥረው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ እንደአግባብነቱ "የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሠራር እና ሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 05/2012" አንቀጽ 8 ስር የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ የሚሰራውን የስራ አይነት እና የስራ ዝርዝር የሚያሳይ መግለጫ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

### አንቀፅ 11. ለመመዝገብ ስለሚቀርብ ጥያቄ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት አንድ ታዛቢ ቡድን የታዛቢነት ፈቃድ ለማግኘት የሚያቀርበው ማመልከቻ ቀጥሎ የተመለከቱትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

   ሀ) የታዛቢው ቡድን መጠሪያ ስም፣ አድራሻ እና ለመገናኛ የሚያገለግሉ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች፣

   ለ) የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድን ኃላፊ ስም፣

   ሐ) የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ ለመታዘብ ያሰበውን የምርጫ ሂደት ፣

   መ) ታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ የወከለው ተጠሪ ስምና ለመገናኛ የሚያገለግሉ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች እና፣

   ሠ) የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ የሚያሰማራቸው ታዛቢዎች ኢትዮጵያ ይገባሉ ተብሎ የሚጠበቅበት ቀን እና ብዛታቸው፡፡

2. ፈቃድ ለማግኘት ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር ቀጥሎ የተመለከቱት ሰነዶች አባሪ ሆነው መቅረብ አለባቸው፣

ሀ) የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ ተጠሪ በተጠሪነት የተሰየመበት እና ሰነዶችን ለመቀበልና ለማቅረብ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለመፈረም እንዲችል በቡድኑ የተወከለበት የተረጋገጠ ሰነድ፣

ለ) የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ ወኪል እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ በመሆን የሚያስማራውን ሰው ማንነት የሚገልጽ ፓስፖርት ቅጂ፣ እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛውን መታወቂያ ወይም ማንነቱን ሊያሳይ የሚችል ሰነድ፣ እንዲሁም ሁለት በቅርቡ የተነሳውና በጀርባው የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ መጠሪያ የተጻፈበት የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፣

ሐ) ታዛቢው ይህንን መመሪያ የሚያከብር ስለመሆኑ የፈረመበት ሰነድ እና ታዛቢው ከታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ በቂ ሥልጠና ያገኘ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣

መ) እንደ አግባብነቱ ህጋዊ ሰውነትን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

ሠ) ምርጫውን ለመታዘብ የመረጡትን የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት፡፡

3. ታዛቢ ተቋም ወይም ቡድኑ የወኪሎቹን የፆታ ተዋፅኦ ለማመጣጠን ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ የሚያቀርበውን የታዛቢዎች ዝርዝር በፆታ ለይቶ ማቅረብ አለበት፡፡ የምርጫ መታዘብ ስልቱም በተመሳሳይ የሥርዓተ-ጾታን እና የሴቶችን ተሳትፎ ታሳቢ ያደርገ መሆን አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ ቦርዱ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 12. በታዛቢ ቡድን ፈቃድ ለማግኘት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ስለሚሰጥ ውሣኔ

1. ቦርዱ ፈቃድ ለማግኘት በሚቀርብለት ጥያቄ ላይ በተቻለ ፍጥነት ውሣኔ ይሰጣል፡፡
2. የምርጫ ሂደትን ለመታዘብ የሚቀርበው የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻውን ለማቅረብ በቦርዱ የተወሰነው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ ከሆነ ወይም ማመልከቻው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ውድቅ ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ በተቻለ ፍጥነት ያልተሟላው ወይም ስህተት ያለው ማመልከቻ እንደገና ተሟልቶ ወይም ታርሞ እንዲቀርብ ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀፅ 13. የታዛቢ የፍቃድ ጥያቄን ስላለመቀበል**

1. የታዛቢ የፈቃድ ጥያቄ በሚከተሉት ምክንያቶች ውድቅ ሊደረግ ይችላል

ሀ) ታዛቢው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ፣

ለ) የሚያሰማራው ታዛቢ ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች ከሆነ፣

ሐ) በከባድ ወንጀል ተጠርጥሮ የሚፈለግ ከሆነ፣

መ) የታወቀ የሥነ ምግባር ብልሹነት ካለው፣

ሠ) የታዛቢው ስም በማንኛውም ሌላ የውጪ፣ የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ቡድን፣ የፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ወኪሎች ዝርዝር ላይ ከተገኘ፣

2. አንድ ታዛቢ ተቋም ወይም ቡድን በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ቢያሟላም ቦርዱ የታዛቢውን ገለልተኝነት ለመጠርጠር አሳማኝ ምክንያቶች ሲያገኝ የፈቃድ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 14. ለታዛቢዎች የመታወቂያ ካርድ ስለመስጠት**

1. በታዛቢው የቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ለተፈቀደለት ታዛቢ ወኪሎች የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ ይዘጋጃል፡፡
2. የመታወቂያ ካርዱ የሚከተሉትን ይይዛል፤

ሀ) የቦርዱን አርማ፣

ለ) የወኪሉን ስም፣

ሐ) የወኪሉን ዜግነት፣

መ) ወኪሉ የሚወክለው የተቋም ስም፣

ሠ) ወኪሉ በቅርቡ የተነሳው ፎቶግራፍ፤

ረ) የቦርዱ ማኅተም፣

ሰ) የመታወቂያ ካርዱ የሚያገለግልበት ጊዜ፣

ሸ) የመታወቂያው ቁጥር፣

ቀ) የቦርዱ ባለሥልጣን ፊርማ።

1. መታወቂያው የታዛቢ ቡድኑ የመጨረሻ ሪፖርቱን ለቦርዱ እስከሚያቀርብ የፀና ይሆናል።

2. የመታወቂያ ካርዶቹ እንደተዘጋጁ የታዛቢ ተቋሙ ወይም ቡድኑ ተጠሪ ወይም ተቋሙ የወከለው ሰው መታወቂያዎቹን ይረከባል። መታወቂያዎቹን ለቡድኑ ታዛቢዎች ይሰጣል።
3. የታዛቢነት ፍቃድ ያገኘ ተቋም ወይም ወኪሉ የመታዘብ ሥራውን ካቋረጠ ወይም ተቋሙ ታዛቢውን ከቀየረ የታዛቢነት መታወቂያውን ተረክቦ ለቦርዱ መመለስ አለበት።
4. ከላይ በንዑስ ቁጥር 2 ስር የተመለከቱትን መረጃዎች የያዘ መታወቂያ እንደአግባብነቱ ታዛቢ ቡድኑ በአስተርጓሚነት ለሚቀጥራቸው አስተርጓሚዎችም የሚሰጥ ይሆናል። በዚህ አንቀፅ ለታዛቢዎች የሚሰጥ መታወቂያ የሚፀናበትን ጊዜ፣ ስለርክክባቸው እና ለቦርዱ ተመላሽ ስለሚሆኑበት ሁኔታ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለአስተርጓሚዎች በሚሰጥ መታወቂያም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 15. ምዝገባ ወይም ፈቃድ የሚሰረዝበት ሁኔታ

1. ቦርዱ በራሱ ወይም በሌላ በማንኛውም አካል በደረሰው ተጨባጭ ጥቆማ መሠረት ለታዛቢ ወይም ለተመዘገበ ታዛቢ ቡድን የሰጠውን የታዛቢነት ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰርዝ ይችላል።

    ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ታዛቢ ለመሆን ከማያበቁ ምክንያቶች አንዱ የተገኘበት ከሆነ፣

    ለ) በማንኛውም ሥልጣን ባለው የምርጫ አስፈጻሚ የተሰጠውን መመሪያና ሕጋዊ ትዕዛዝ ካላከበረ፣

    ሐ.) ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ዕጩ ወገንተኝነትን በግልጽ ካሳየ፣

    መ) የአንድን የምርጫ አስፈፃሚ ተግባር ካደናቀፈ ወይም ካሰናከለ፣

    ሠ) ይህንን መመሪያ፣ ሌሎች ሕጎችንና ደንቦችን ከጣሰ።

2. ቦርዱ የታዛቢ ቡድኑ ፈቃድን ወይም ለታዛቢ ቡድኑ ወኪል የሰጠውን መታወቂያ ከመሰረዙ በፊት የታዛቢ ቡድኑ ተጠሪ ወይም ወኪል በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ እድል ይሰጠዋል፡፡
3. ቦርዱ የታዛቢ ቡድኑን አስተያየት ከሰማ በኋላ ለቡድኑ ወኪል የተሰጠውን ፈቃድ ከሰረዘ ይህንኑ ለሚመለከተው የቡድኑ ተጠሪ ወይም ወኪል ያሳውቃል፡፡ ፈቃድ የተሰረዘበት ታዛቢ የተሰጠውን የመታወቂያ ካርድ ወዲያውኑ በቡድኑ ወይንም በተጠሪው በኩል ለቦርዱ መመለስ አለበት፡፡
4. ቦርዱ በውሳኔው የታዛቢ ቡድኑን ወይም የታዛቢውን ፈቃድ የተሰረዘበትን ምክንያት መግለጽ አለበት፡፡
5. የውጪ ታዛቢ ቡድን ወይም ተቋም የታዛቢው ፍቃድ መሰረዝ ላይ ቅሬታ ካለው በቡድኑ መሪ ወይም በተጠሪው አማካኝነት ቅሬታውን ለቦርዱ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## <u>የታዛቢ ተቋም ወይም ቡድን እና የታዛቢዎች መብቶች እና ግዴታዎች</u>

### አንቀፅ 16. የምርጫ ታዛቢዎች መብት

ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ፦

1. አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በሚሰጥ ከፀጥታ ወይም ደህንነት ጋር በተያያዘ በግልጽ በተመለከተ ምክንያት በተሰጠ ምክር ካልሆነ በስተቀር በቅድሚያ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ወይም ማሳወቅ ሳያስፈልገው በአገሪቱ ማንኛውም ቦታ በመዘዋወር የምርጫ ሂደቱን የመታዘብ፣
2. ከደህንነት ወይም ከፀጥታኝ ጋር በተገናኘ የሚገጥመውን ማንኛውንም አሳሳቢ ጉዳይ በሚመለከት እርዳታ ሲያስፈልገው ከቦርዱ፣ ከሚመለከታቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የአካባቢ ባለሥልጣናት በጊዜው እርዳታ ጠይቆ የማግኘት፣
3. በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል እና የክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
4. የምርጫ ሰነዶችን የመመልከት፤ የድምጽ አሰጣጥ እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን የመታዘብ፣

5. በምርጫው ሂደት የታዘባቸውን ወይም ያጋጠሙትን ጉድለቶች ለቦርዱ ወይም በየደረጃው ላሉ የቦርዱ ጽ/ቤቶች የማቅረብ፣
6. ከማንኛውም መንግስታዊም ሆነ ሌላ ተቋም ወይም ሰው ተፅእኖ ነፃ የመሆን፣
7. ምልከታውን፣ ትዝብቱን፣ ግኝቱን እና የደረሰበትን ድምዳሜ አስመልክቶ ለህዝብ ይፋ መግለጫ የመስጠት መብት አለው፣

**አንቀጽ 17. የምርጫ ታዛቢዎች ግዴታ**

1. የምርጫ ታዛቢዎች የሚከተሉት ግዴታዎችን ማክበር አለባቸው፡፡

ሀ) የአገሪቱን ሉአላዊነት ማክበር፣

ለ) የምርጫ አዋጁን፣ መመሪያዎችና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ማወቅ፣ የአገሪቱን ሕጎችና ቦርዱ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች ማወቅና ማክበር፣

ሐ) በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፣

መ) በማንኛውም ጊዜ እና ሁኔታ የጦር መሣሪያ አለመያዝ፡፡

ሠ) ቦርዱ የሚያዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር ደንብ መፈረም፡፡

2. ማንኛውም ታዛቢ በዚህ መመሪያ የተካተተውን የሥነ ምግባር ደንብ ለማክበር የገባውን ስምምነት ለመጣሱ ቦርዱ በራሱ ወይም በሌላ በማንኛውም አካል በደረሰው ጥቆማ መነሻ መጣሱን ያረጋገጠ እንደሆነ፣

ሀ. ታዛቢ ተቋሙ ወይንም ቡድኑን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ምክር መስጠት ወይም ማስጠንቀቅ፣

ለ) እንደጥፋቱ ክብደት የተሰጠውን የመታዘብ ፈቃድ መሰረዝ፣

ሐ) ጥፋቱ በሌላ ህግ መሠረት በወንጀል የሚያስጠይቅ ከሆነ ለሚመለከተው አካል መምራት ይችላል።

**አንቀጽ 18. ሙያዊ ሥነ ምግባርና መልካም ጠባይ ስለማሳየት**

ታዛቢዎች በስራም ሆነ ከስራ ሰዓት ውጪ፡-

1. ለአገሪቱ ሕዝቦችና ባሕሎች አክብሮት ማሳየት፣
2. መልካም የግል ፀባይ ማሳየትና ሌሎችንም ማክበር፣
3. ምርጫውን በተመለከተ ሚዛናዊ ሃተታ መስጠት፣
4. የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ከፍተኛ ሙያዊ ሥነ ምግባር የተላበሱ መሆን አለባቸው።

**አንቀጽ 19. የመታወቂያ ካርድን ስለማሳየት**

ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢዎች፡-

1. በምርጫ መታዘብ ተግባር በተሰማሩበት ጊዜ ሁሉ ከቦርዱ የተሰጣቸውን የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ እና አርማ (ባጅ) በግልጽ ሊታይ በሚቻልበት ሁኔታ በደረታቸው ላይ ማድረግ አለባቸው።
2. ሥልጣን ባለው አካል ሲጠየቁ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ካርድ እና አርማ(ባጅ) ወዲያውኑ ማሳየት አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 20. የታዘቡትን ጉዳይ ትክክለኛነት እና የሚደርሱበትን ድምዳሜ ሙያዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት**

የታዛቢ ቡድኖች፡-

1. ሀሳብ የሚሰጡት ወይም ድምዳሜ ላይ የሚደርሱት በተገቢው ማስረጃ ላይ በመመስረት፣ እውነታን ከግላዊ አመለካከት በመለየትና ገለልተኛ ትንታኔ በማድረግ መሆን አለበት፡፡
2. አስፈላጊ የሆኑትንና ያልሆኑትን ጉዳዮች በመለየት እና በምርጫው ተአማኒነት ላይ ከፍተኛ እንደምታ ሊኖራቸው በሚችል ጉዳዮች ላይ በማተኮር ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ምርጫውን መታዘባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. የሚደርሱበትን ድምዳሜ በሙሉ ሊረጋገጥ በሚችል ተጨባጭ ማስረጃ ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ ለቅሬታ ምክንያት የሆነ አንድ ጉዳይ ካጋጠማቸው ድምዳሜ ላይ ከመድረሳቸው በፊት የጉዳዩን ሂደት በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው፡፡

4. የምርጫ ሂደትን በሚመለከት የተደረጉ መደምደሚያዎችን ወይም ግኝቶችን በማስረጃ ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለባቸው፡፡ ተከስቷል ተብሎ የተገለጸን አንድ ጉዳይ ማረጋገጥ ካልተቻለ ታዛቢው በሪፖርቱ ላይ ጉዳዩን ለማረጋገጥ አለመቻሉን በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡
5. የሚከተሉትን የአሠራር መንገድ መግለጽ አለባቸው፡፡
6. መረጃ በሥርዓት፣ ግልጽ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ የተሰበሰበ፣ የተጠናቀረና የታተመ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
7. በምርጫ መታዘብ ሂደት የሚሰበስቡት፣ የሚጠቀሙበት ወይም የሚያትሙት መረጃ በቀጥታ ያገኙትና በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለባቸው፡፡
8. የምርጫ አስፈጻሚዎችን ወይም ማንኛውም የምርጫ ሂደቱ ተሳታፊ የሆነን አካል በሚመለከት አሉታዊ የሆነ አስተያየት ከመቀበላቸው በፊት ጉዳዩ ከሚመለከተው የቦርዱ አካል አስተያየት ወይም መልስ ለመቀበል አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 21. የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሪፖርት መቅረብ ያለበት በሚከተለው አኳኋን ነው፡-

1. ማንኛውም ታዛቢ ለወከለው ቡድን ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ የተሰማራበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት ከተገለጸ በኋላ በወከለው ቡድን የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ታዛቢ ቡድን ከመጨረሻ ሪፖርቱ አስቀድሞ የሚያዘጋጀውን ቀዳሚ ሪፖርትን የሚመለከት መግለጫ ከምርጫው ቀን አጭር ጊዜ በኋላ በማናቸውም ጊዜ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ይችላል፡፡ የቀዳሚ ሪፖርቱን መሠረት በማድረግ የሚያወጣቸው ማናቸውም መግለጫዎች በታዛቢ ቡድኑ የቀረበውን ቀዳሚ ሪፖርትን አስመልክቶ የተሰጡ እንጂ የመጨረሻ ሪፖርትን መሠረት ያደረጉ እንዳልሆነ በግልፅ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም ታዛቢ ቡድን ስለታዘበው የምርጫ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ቦርዱ የምርጫውን ውጤት ይፋ ካደረገበት ቀን በኋላ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ይችላል፡፡ የመጨረሻ ሪፖርቱን ለህዝብ ይፋ ከማድረጉ አስቀድሞ

ሪፖርቱን ለቦርዱ የማቅረብ በሪፖርቱም ላይ ከቦርዱ ጋር አስፈላጊውን ውይይት ማድረግ ይኖርበታል።

የሪፖርቱ ይዘትም፦

ሀ) ቡድኑ በምርጫ ታዛቢነት ሥራው የሸፈነው ክልል፣ ዞን፣ የምርጫ ክልል ወይም ምርጫ ጣቢያ ብዛት እና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውን፣

ለ) የፆታ ተዋፅኦ፣ የአካል ጉዳተኝነት እና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የህብረተሰቡ ክፍሎች ተሳትፎ፣ ተግዳሮቶች እና መፍትሄ ሃሳቦች እና ፣

ሐ) በእያንዳንዱ የምርጫ እንቅስቃሴ ሂደት፣ በምርጫ ዝግጅት፣ በመራጮች ምዝገባ፣ በእጩዎች ምዝገባ፣ በምርጫ ዘመቻ፣ በድምፅ አሰጣጥ፣ በድምፅ ቆጠራ እና በውጤት አገላለፅ ላይ የታዘባቸውን ሁኔታዎችና የተጠቀመባቸው መረጃዎች ያካተተ መሆን አለበት።

## ምዕራፍ አራት

## የውጪ የምርጫ ታዛቢዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 22. የምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጣን ማክበር

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ታዛቢ፦

1. የቦርዱን እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ የፀጥታና ደህንነት እንደዚሁም የሌሎች የመንግስት አካላት የሚሰጡትን ህጋዊ ትዕዛዝና መመሪያ መቀበልና ማክበር፣
2. ከምርጫ አስፈፃሚዎች እንደዚሁም ከሌሎች ታዛቢዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት አለበት።

## አንቀጽ 23. ምክር ስላለመስጠት

ማንኛውም ፍቃድ የተሰጠው የምርጫ ታዛቢ፡-

1. ለምርጫ አስፈፃሚዎች ከኃላፊነታቸው ጋር የተያያዘ መመሪያ ወይም ምክር መስጠት፣
2. የተከሰቱ ችግሮችን የአፈታት ሂደት ከመታዘብ ውጭ የውይይቱ አካል በመሆን በቅሬታ /አቤቱታ/ አፈታት ሂደት ውስጥ መሳተፍ የለበትም፡፡

## አንቀፅ 24. ገለልተኛ ስለመሆን

ፍቃድ የተሰጠው የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ፡-

1. ተግባራቱን ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን ማከናወን፤ ከማንኛውም አካል ጋር በማንኛውም ሁኔታ ገለልተኝነቱን ከሚጎዳ ወይም ወገንተኝነትን ከሚያሳይ እንቅስቃሴ መቆጠብ አለበት፡፡
2. የፖለቲካ ድርጅቶች ወይም ግል እጩዎች በሚያዘጋጇቸው ፕሮግራሞች ላይ መገኘት የሚችሉ ቢሆንም ለፖለቲካ ፓርቲዎችወይም እጩዎች ወገንተኝነት ሊገልፅ ከሚችል በእነዚህ አካላት ወይም ሰዎች ከተዘጋጀ የጉብኝት፣ የግብዣ ወይም ሌላ መሰል እንቅስቃሴዎች ላይ ከመሳተፍ መታቀብ አለበት፡፡
3. ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲወይም እጩን ከመደገፍ ወይም ከመንቀፍ መቆጠብ፤ ከባለስልጣናት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከእጩ ተወዳዳሪዎች ከመራጮችና ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዘ ወይም አወዛጋቢ በሆነ የምርጫ ጉዳይ ላይ ወገንተኝነትን ከማሳየት ወይም ከመግለጽ መታቀብ አለበት፡፡
4. የማንኛውንም በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ የፖለቲካ ፓርቲን ወይም እጩን፣ ማንኛውንም ዓይነት ምልክት ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ በግቢው፣ በቢሮው፣ በመጓጓዣው፣ በራሱ ላይ እንደሁኔታው በማሳየት፣ በመያዝ፣ በማስቀመጥ፣ በመስቀል፣ በመለጠፍ ወይም በመልበስ በመሳሰለው ሁኔታ መንቀሳቀስ፣ ማሳየት ወይም ይዞ መገኘት የለበትም፡፡

## አንቀጽ 25. የምርጫን ሚስጥራዊነት እና የመራጮችን መብት ስለማክበር

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ፡-

1. መራጩ ድምፁን ለማን እንደሰጠ ወይም ማንን እንደሚመርጥ መጠየቅ፣
2. በሚታዘብበት ወቅት የምርጫ ሂደቱን በሚያውክ ሁኔታ የምስል እና የድምፅ መቅረጫ መሳሪያ መጠቀም፣
3. መራጭ ድምፅ በሚስጢር የሚሰጥበት ክፍል ወይም ለዚሁ የተከለለ ቦታ መግባትም ሆነ ካሜራም ወይም ሌላ የድምፅ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ መጠቀም፣
4. ማንኛውንም ለመመዝገብ ወይም ድምፅ ለመስጠት የተገኘን ሰው ወይም የምርጫ አስፈፃሚ ያለፈቃዱ ወይም በግልፅ እየተቃወመ በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም ቃለ-መጠይቅ ማድረግ፣
5. የመራጮች ምዝገባ መረጃዎች በሰነድ ላይ ሲሰፍሩ ወይም መራጩ በድምፅ መስጫው ወረቀት ላይ የምርጫ ምልክት ሲያደርግ፣ በግልጽም ሆነ ተደብቆ በፊልም መቅረጽ ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት፣
6. የድምፅ ሰጪዎችን የግላዊነት መብት በሚነካ አኳኋን የመራጮችን መዝገብ፣ የመራጮችን ምዝገባ መታወቂያ ወይም ማናቸውንም ሌላ ሰነድ በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም ኮፒ ማድረግ የለበትም፡፡

## አንቀፅ 26. ጥቅም አለመቀበል ወይም አለመስጠት

ማንኛውም የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ ከማንኛውም በምርጫ እንቅስቃሴ ከሚሳተፍ የፖለቲካ ፓርቲ፣ እጩ፣ ደጋፊ ወይም ሰው ወይም አካል በምርጫ ሂደት ማንኛውንም ተግባር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ወይም በደጋፊነት ለመንቀሳቀስ በማሰብ ጥቅም መቀበል ወይም መስጠት፣ ለመቀበል ወይም ለመስጠት መዋዋል ወይም ቃል መግባት የለበትም ፡፡

## አንቀፅ 27. የጥቅም ግጭት

1. ማንኛውም ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ፡-

   ሀ) የምርጫ ሂደትን ከመታዘብ ተግባሩ ጋር በተያያዘ ያጋጠመው የጥቅም ግጭትን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ) የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ወይም ሊያስከተል በሚችል በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ መሣተፍ የለበትም፡፡

2. በምርጫ ታዛቢነት ሥራው ላይ በንብረት፣ በገንዘብ፣ በዝምድና ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች ያጋጠመው ወኪሉ ሲሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራበት አካባቢ የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት እና ላሰማራው ታዛቢ ቡድን፤ ታዛቢ ቡድኑ ሲሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራበት አካባቢ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እና ለቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የጥቅም ግጭት አጋጥሞት ወይም እንደሚያጋጥመው በማወቁ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀረበ ሰው የታዛቢነት ሥራውን አቋርጦ ቦርዱ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠባበቅ ይኖርበታል፡፡
4. ቦርዱ በዚህ አንቀፅ መሠረት የጥቅም ግጭት ካጋጠመው ሰው ወይም ከሚመለከተው የምርጫ አስፈፃሚ ሪፖርት ሲደርሰው ጉዳዩ ነፃ፣ ቀጥተኛና ፍትሃዊ ምርጫን የሚያደናቅፍ እና የማያደናቅፍ መሆኑን በራሱ በማጣራት በቦታው ላይ ሥራውን እንዲቀጥል ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከታዛቢነቱ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡ ውሳኔውንም ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

**አንቀፅ 28. ሀቀኝነት**

ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ቡድንም ሆነ ቡድኑ የሚያሰማራው ተወካይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 እና 20 በተደነገገው መሰረት፦

1. በማንኛውም ጊዜ የሚያቀርበው ወይም የሚያሰራጨው መረጃ ወይም ሪፖርት ሀቀኛ፣ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ግልፅና የማያሻማ መሆን አለበት፡፡
2. ያቀረበው ወይም ያሰራጨው ሪፖርት ወይም መረጃ ተቀባይነት ባለው አሰራር የተሰበሰበ፣ የተጠናቀረ፣ የታተመ እና የተፈረመበት መሆን አለበት፡፡

**አንቀፅ 29. ቅንነት**

1. ማንኛውም የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢው የታዛቢነት ተግባሩን የሚያከናውንበት ሂደት ቅንነት የተሞላበት ሥነ ምግባር ሊኖረው ይገባል፡፡

2. ታዛቢው የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥመው ጉዳዩን ወዲያውኑ ላሰማራው ታዛቢ ቡድን ተጠሪ ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀፅ 30. ስለትብብርና ወጪን ስለመሸፈን

1. ቦርዱ፡-

ሀ) ለታዛቢ ቡድኖችና ለሚያሰማሯቸው ታዛቢዎች የሚችለውን ትብብር ሁሉ ለማድረግ እና በጥያቄያቸው መሠረትም ምሥጢራዊ ያልሆነ መረጃን ሁሉ ለመስጠት ጥረት ያደርጋል፡፡

ለ) በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች ሥልጣናቸው በሚፈቅደው መጠን የምርጫ ታዛቢዎች በዚህ መመሪያና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች የተመለከተው ተግባራቸውን ለማከናወን እንዲችሉ እገዛ እንዲያደርጉላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸዋል፡፡

2. እያንዳንዱ ታዛቢ ቡድን ወጪውን በሙሉ እራሱ ይሸፍናል፡፡ ፈቃድ ለተሰጣቸው ወኪሎቹም በኢትዮጵያ ለማሰማራት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
3. እያንዳንዱ ታዛቢ ቡድን ከመታዘብ ተግባሩ ጋር በተያያዘ ለመጓጓዣ፣ ለመገናኛ እና ለሆቴል የሚያስፈልገውን ወጪ እና ሌላ ድጋፍ በተመለከተ ቡድኑ ብቸኛ ኃላፊ ነው፤ ቦርዱ ለማንኛውም ወጪ ኃላፊነት የለበትም፡፡ እንዲሁም፣ ማንኛውም ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢ በማናቸውም የቦርዱ፣ የመንግስታዊ ተቋም ወይም የተወዳዳሪ ፖሊቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ንብረት በሆነ እንደ መኪናና ሌሎች መገልገያዎች ሊጠቀም አይችልም፡፡

## አንቀጽ 30. ስለምርጫው ውጤት አስቀድሞ አስተያየት መስጠት ስለመከልከሉ

ማንኛውም የውጪ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ወይም ታዛቢው የምርጫ ውጤት አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ በአንቀፅ 20 ንዑስ ቁጥር 2 ስር የታዛቢ ቡድን ቀዳሚ ሪፖርት አቀራረብን አስመልክቶ ከተደነገገው አኳኃንውጪ በቦርዱ በይፋ ውጤት ከመገለጹ በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ሆኖ ይፋዊ አስተያየት ወይም መግለጫ መስጠት አይችልም፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 31. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ይህ መመሪያ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 32. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ